# 9ኛ ትምህርት

ህዳር 10-16 2009 ዓ.ም Nov 19 — 25

## ተስፋው ሲገለጥ

### ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡-** ምሳሌ 17፡28፣ ኢዮብ 13፡1-15፣ ያዕቆብ 2፡20-22፣ 1 ቆሮ. 15፡11-20፣ 1ኛጴጥ. 1፡18-20፣ ዘፍ. 22፡8።

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ግብዝ ሰው በእርሱ ፊት መቅረብ ስለማይችል እርሱ መድሃኒቴ ይሆንልኛል።" ኢዮብ 13፡16

እ ንግሊዛዊው ፀሐፊ ሄዝሊት "ሰው አንድ ነገር መሆን ባለበትና በትክክል እየሆነ ባለው መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚያውቅ ብቸኛው የሚስቅና የሚያለቅስ እንስሳ ነው።" ብሎ ፅፎ ነበር።

በእርግጥም እየሆነ ያለው በትክክል መሆን ያለበት አይደለም። ሆኖም የዳግም ምፃቱን ተስፋ ለያዘ ክርስትያን ግን ተስፋ አለ፡- ነገሮች እንዴት በድንቅ እንደሚለወጡ የሚያስረግጥ ታላቅ ተስፋ /2ኛጴጥ. 3፡ 13/። በዚህ በኃጢአት በጨለመ አእምሮ /1ኛቆሮ. 13፡12/ ልንገምት ከምንችለው በላይ እጅግ አስደናቂ ነገሮች ይሆናሉ። በመመራመር ብቻ ልኑር የሚለው አእምሮ ከመጥበቡ የተነሳ ሊረዳ ያልቻለው ይህንን ተስፋ ነው።

በዚህ ሳምንት በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ የመከራን ጥያቄ መመርመራችንን ስንቀጥል ከደረሰበት አሳዛኝ ትርጉም አልባና ያልተገለጠ መከራ በተቃራኒ ኢዮብ የተስፋ ቃላትን ሲናገር እንሰማዋለን።

**ያ ተስፋ ምን ነበር? እኛም ተስፋ እንድናደርግበት ምን ይነግረናል?**

**የዚህ ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለህዳር 17 ሰንበት ይዘጋጁ።**

*እሁድ ህዳር 11* *Nov 20*

## በሐሰት ለባጮች

"ሰነፍ ዝም ቢል ጠቢብ ሆኖ ይቆጠራል፤ ከንፈሩንም የሚቀልፍ ባለ አእምሮ ነው ይባላል።" ምሳሌ 17፡ 28 አንድ ሰው ስለ ኢዮብ የፈለገውን ቢናገር በዚያ መከራና ስቃይ ሆኖ ጓደኞቹ የሚናገሩትን ሁሉ በዝምታ መቀበል አለበት ማለት አይችልም።በተቃራኒው የኢዮብ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል ኢዮብ ለተሰነዘሩበት የእውነትና የስህተት ቅልቅል ቃላት የተሟገተውን ሙግት የያዘ ነው። እንዳየነው እነዚህ ሰዎች በጥበብና በርህራሄ እየተናገሩ አይደለም። በኢዮብ ላይ ስለተፈጠረው ነገር እግዚአብሔርን እንደወከሉ ሆነው እየተናገሩ ነበር። እናም ኢዮብ የሚገባውን / የእጁን/ እያገኘ እንደሆነ ከዚያ በላይ ሊሆንበት ይገባ እንደነበር ተናገሩ። ከላይከተጠቀሱት ቃላት አንዱን መናገር ብቻውን በቂ ነበር፤ ሆኖም ይህንን ሁሉ ከዚህም በላይ ጨምረው ሲናገሩ ኢዮብ መልስ ሰጥቷል።

**ኢዮብ 13፡1-14ን ያንብቡ። ለተሰነዘረበት ጥቃት ኢዮብ በምን መልኩ ምላሽ ሰጠ?**

---

---

በምዕራፍ ሁለት እንደምንመለከተው እነዚህ ሰዎች ኢዮብን መጥተው አይተውት ለሰባት ቀናት አልተናገሩትም። ቀስ በቀስ ከአፋቸው መውጣት ከጀመረው ነገር አንፃር ይህ የተሻለ ምላሽ ሊሆን ይችላል፡ ፡ ኢዮብ ያሰበው በእርግጥም ያንኑ ነው። ኢዮብ ሲናገር እነዚህ ሰዎች ውሸት ስለማውራታቸው ብቻ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ ነገር መናገራቸውን መግለፁን ልብ እንበል። (በመፅሐፉ ፍፃሜ ብርሃን ስንመለከት ያ የሚያስገርም ነው፡- ኢዮብ 42፡7) ። በእርግጥም የተሳሳተ ነገርን ከመናገር ዝም ማለት

ይሻላል (የዚህን ነገር እውነትነት ከኛ መካከል ያልተለማመደ ማን አለ?) ። ሆኖም ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ ነገርን መናገር የበለጠ የከፋ ነው። እነዚህ ሰዎች ኢዮብ በደረሰበት ነገር ላጉረመረመው በእግዚአብሔር በኩል የቆሙ መስሏቸው ነበር። ኢዮብ እነዚያ ነገሮች ለምን በእርሱ ላይ እንደመጡ ባይገባውም እነዚህ ሰዎች የተናገሩት ነገሮች "የሐሰት ለባጮች" እንዳደረጋቸው ጠንቅቶ አውቋል። (ኢዮብ 13፡4)

**እርስዎ መባል የሌለባቸውንና ስህተት የሆኑ ነገሮችን በቅርብ የተናገሩት መቼ ነበር?**

**ተመሳሳይ ስህተት እንዳይሰሩ ከዚያ ልምምድ የሚማሩት እንዴት ነው?**

*ሰኞ ህዳር 12* *Nov 21*

## ቢገለኝ እንኳን

ይህንን ሩብ አመት ስንጀምር ወደ ኢዮብ መጽሐፍ መጨረሻ ሄደን የኢዮብ ታሪክ ቀስ በቀስ እንዴት እንዳማረ ተመልክተናል። የነበረበት ሁኔታ ምንም ያክል ከባድ ቢሆን ኢዮብ ተስፋ የሚያደርግበት ነገር ነበረው። በእርግጥም አሁን ባለንበት ጊዜ ስንኖርና የመፅሐፍ ቅዱስን ታሪክ ፍጻሜ ስለምናውቅ ኢዮብ ከዚያ ጊዜ ይልቅ አሁን ብዙ ተስፋ ሊያደርግ የሚችልበት ነገር እንደነበረው መመልከት እንችላለን።

ሆኖም ልጆቹ ሲሞቱ፣ ንብረቱ ሲወድምና ጤናው ሲታወክ ኢዮብ ነገሮች እንዴት እንደሚስተካከሉ የሚያውቅበት ምንም ሁኔታ አልነበረም። የሚያውቀው ህይወቱ በድንገት እንደተገለባበጠ ብቻ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢዮብ አለመወለዱን ቢመኝም ተወልዶ ወደ መቃብር መውረድን ተመኝቶ ቢያማርርም ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እያኖረው እንዳለ በሚያስበው በአምላኩ በእግዚአብሔር ተስፋውን ይገልጽ ነበር፡ ፡

**ኢዮብ 13፡15ን ያንብቡ። በዚህ ጥቅስ ላይ የተገለፀው ተስፋ ምንድነው? ኢዮብ እያለ ያለው ምንድነው?**

---

‹‹ቢገለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ›› ኃይለኛ የእምነት መግለጫ! ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢዮብ በርሱ ላይ ያልደረሰው ብቸኛው ነገር ማለትም ሞት ሊመጣበት እንደሚችል እግዚአብሔርም ሊያመጣበት እንደሚችል አውቋል። ይህ ሁሉ ቢሆን እንኳን ኢዮብ በእግዚአብሔር በመተማመን ሊሞት ወስኗል።

‹‹የክርስቶስ ፀጋ በረከቶችን በአእምሯችን ልናሰላስላቸው ይገባል። ከርሱ ፍቅር የምናገኘውን ትምህርት ገንዘባችን ልናደርገው ይገባል። ‹‹ቢገለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ›› ብለው እስኪያውጁ ድረስ እምነትዎ እንደ ኢዮብ ይሁን። የሰማያዊው አባትዎ ተስፋዎችን ይጠማጠሙ፤ ለርስዎና ለርሱ አገልጋዮች አስቀድሞ ያደርግ የነበረውን ያስታውሱ። ምክንያቱም ‹‹እግዚአብሔርን ለሚወዱት ሁሉም ነገር ተያይዞ ለመልካም" ስለሚሆን ነው።" Ellen G white, The advent Review and Sabbath Herald, October 20,1910

ከንፁህ ሰብአዊ እይታ ኢዮብ ምንም ነገር ላይ ተስፋ ለማድረግ ምንም ምክንያት የለውም ነበር። እውነታው ግን ኢዮብ በንፁህ ሰብዓዊ እይታ ለማየት አልፈቀደም ነበር። እንዲያ ቢያደርግ ኖሮ ምን ተስፋ ይኖረው ነበር? በምትኩ እንደዚህ አይነቱን እምነትና ተስፋ ሲገልፅ በእግዚአብሔርና በእርሱ በመተማመን አውድ ነው የገለፀው።

**ትክክለኛው ጥያቄ፡- ኢዮብ ያ ሁሉ ነገር በእርሱ ላይ መጥቶ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ማጽናት የቻለው እንዴት ነበር? ኢዮብ 1፡1ንና ያዕቆብ 2፡20- 22ን ያንብቡ። እነዚህ ጥቅሶች ለጥያቄው መልስ የሚሰጡት እንዴት ነው?**

**የምንሰጠው መልስ በክርስትና ህይወት ጉዞ ታማኝነትና ታዛዥነት ምን ያክል ጠቃሚ እንደሆኑ ምን ይነግረናል?** (13ኛውን ትምህርት ይመልከቱ)

## ተስፋው ሲገለጥ

**‹‹ግብዝ ሰው በእርሱ ፊት መቅረብ ስለማይችል እርሱ መድሃኒቴ ይሆንልኛል፡፡›› (ኢዮብ 13፡16) ይህ ጥቅስ ትናንት ካነበብነው ጥቅስ ቀጥሎ የመጣነው፡፡ ከምንም በላይ ኢዮብ ተስፋ እንደነበረው እና ተስፋውም በእግዚአብሔር እንደነበር ይህ ጥቅስ የሚያረጋግጥልን እንዴት ነው?**

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው ጥቅስ ቀጥሎ የመጣ ግሩም ስንኝ! ቢሞትም፣ እግዚአብሔር ቢገድለውም ኢዮብ ለመዳኑ በአምላኩ መተማመኑን ቀጠለ፡፡ በአንድ መልኩ እንግዳ ንጽጽር ቢሆንም በሌላ መልኩ በትክክል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ደግሞስ መዳን ማለት ከሞት ነጻ መውጣት ማለት አይደል? ሞትስ ቢያንስ ለዳኑት በኋላ በትንሳኤ የሚታጀብ ጥቂት የሽለብታና የእረፍት ጊዜ አይደል? ታዲያ ይህ ለዘላለም ህይወት የመነሳት ተስፋ በዘመናት ሁሉ ለነበሩት ክርስቲያኖች ታላቁ ተስፋ አይደለምን? ይህ የኢዮብም ተስፋ ነበር፡፡

**1ኛቆሮ. 15፡11-20 ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ቦታ የተሰጠን ተስፋ ምንድን ነው? ያለዚህ ተስፋ ተስፋቢሶች የምንሆነው ለምንድነው?**

______________________________________________________________________________

ከዚህ ጠንካራ የእምነት ማረጋገጫ በኋላ ኢዮብ “ግብዝ በእርሱ ፊት መቅረብ አይችልም” ይላል፡፡ ዋናው የእብራይስጡ ስርወ ቃል “ክብር የማይሰጥ” ወይም “ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለው” የሚል አሉታዊ አንድምታ ያለው ነው፡፡ ኢዮብ መዳን የሚገኘው ለእግዚአብሔር እራስን ሙሉ ለሙሉ በታማኝነት በማስረከብ ህይወት ውስጥ ብቻ እንደሆነ አውቋል፡፡ ለዚያ ነው ክፉውና ግብዙ ሰው ያ ተስፋ የሌለው፡፡ ኢዮብ “የመዳኑን ዋስትና” እየገለፀ ያለ ይመስላል፡፡ ኢዮብ ለኃጢያት የእንስሳት መስዋዕትን ቢያቀርብም

የመስዋዕቱን አስፈላጊነት ምን ያክል እንደተረዳው መናገር አንችልም፡፡ ከመስቀሉ በፊት እንደ ኢዮብ ያሉ አብዛኞቹ ታማኝ የጌታ ተከታዮች ስለ መዳን ልክ እኛ ከመስቀሉ በኋላ የምንኖር ሰዎች እንዳለን አይነት መረዳት አልነበራቸውም፡፡ ሆኖም ኢዮብ የመዳኑ ተስፋ በጌታ ብቻ የሚገኝ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አውቋል፡ ፡ እነዚም መስዋዕቶች መዳኑ እንዴት እንደሚገኝ መግለጫ እንደሆኑ አስተውሏል፡፡

*ረቡዕ ህዳር 14* *Nov 23*

## ተስፋ፡ ዓለም ከመፈጠሯ በፊት

ከኛ መካከል ኢዮብ ባለፈበት መከራ አልፎ እንዲህ አይነት ኃይለኛ የተስፋ ቃላትን የሚናገር ማን ይሆን? የርሱ ቃላት የእምነትና የመታዘዝ ህይወቱ ዘላለማዊ ምስክሮች ናቸው፡፡

ኢዮብ ባለተስፋ የነበረው ተስፋ የሚሰጥ አምላክን ስለሚያመልክ ነው፡፡ በኤደን ከአዳምና ሔዋን ውድቀት ጀምሮ (ዘፍጥረት 3) እስከ መጨረሻው የባቢሎን ውድቀት (ራዕይ 14:8) ድረስ ብዙ ደስ የማይሉ የኃጢያት ታሪኮችን ብንሰማም መፅሐፍ ቅዱስ ይህቺ ምድር ልትሰጠን ከምትችለው ባለፈ በተስፋ የተሞላ መፅሐፍ ነው፡፡

“ዓለም ለክርስቶስ ተሰጥታለች፤ ከእግዚአብሔር ወደ ወደቀው ሰብአዊ ዘር የመጣው ተስፋ በክርስቶስ በኩል ነው፡፡ ልክ ስጋ ከለበሰ በኋላ እንደሆነው ሁሉ ስጋ ከመልበሱ በፊትም ቤዛችን ነበር፡፡ ልክ ኃጢአት እንደመጣ አዳኝም ተዘጋጅቷል፡፡” Ellen G. white, the desire of ages, p.210 ከተስፋችን ታላቁ ምንጭ ውጪ ሌላ ማን አዳኝ አለ?

እነዚህ ጥቅሶች በዛሬው ክፍል ላይ በተጠቀሰው የኤለን ጂ. ኋይት ዓረፍተ ነገር

**ውስጥ የተገለጠውን ታላቅ ተስፋ የሚያረጋግጡት እንዴት ነው? ኤፌ. 1፡4፤ ቲቶ 1፡2፣ 2ጢሞ. 1፡8-9፣ 1ኛጴጥ.1፡18-20**

እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ነገሮች ከመሆናቸው አስቀድሞ ስለሚያውቅ አለምነከመፈጠሩ በፊት እንኳ የሰው ልጅ እንደሚወድቅ ያውቅ እንደነበር ያስተምራሉ፡፡ 2ኛ ጢሞ. 1፡9 በግሪኩ እንደሚናገረው "ጊዜ ከመፈጠሩ በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ በተሰጠን ፀጋ ተጠርተናል፡፡ ይህ ፀጋ "እንደስራችን" የተሰጠን ሳይሆን በኢየሱስ የሆነልን ነው፡፡ (መጀመሪያውኑ ወደ መኖር ሳንመጣ እንዴት እንደስራችን ሊሆን ይችላል?) ገና ከመፈጠራችን በፊት ለሰው ልጅ የዘላለም ህይወት ተስፋን የሚሰጠውን እቅድ እግዚአብሔር አዘጋጀ፡፡ ይህ ተስፋ እኛ ከፈለግነው በኋላ የመጣልን ሳይሆን ልክ ባስፈለገን ጊዜ እንድንወስደው አስቀድሞ ተዘጋጅቶልን ነበር፡፡

እንደ ክርስቲያንነታችን ብዙ ተስፋ የምናደርግባቸውና የምንተማመንባቸው ነገሮች አሉ፡፡ የምንኖረው በሚወደን (ዮሐ. 3፡16) ፣ በተቤዠን (ቲቶ 2፡14) ፣ ጸሎታችንን በሚሰማው (ማቴ. 6፡6) ፣ በሚማልድልን (ዕብ. 7፡25) ላይተወን ቃል በገባልን (ዕብ. 13፡5) ፣ ከሞት ሊያስነሳን ተስፋ በሰጠን (ኢሳ. 26፡19) እና ከእርሱ ጋር የዘላለም ሕወት ሊሰጠን ቃል በገባልን አምላክ በተፈጠረ አለም ነው፡፡

**"እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል" (ሮሜ 8፡31)**

**እርስዎ በዚህ ሰአት በተለያዩ ነገሮች ውስጥ እያለፉ ቢሆንም ይህንን ተስፋ የግልዎ ማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው?**

## የተስፋው ምስሎች

**ቀጥሎ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ያንብቡ። እያንዳንዳቸው የሚሰጡዎት ተስፋዎች ምንድናቸው?**

ዘፍ. 3፡15

ዘፍ. 22፡8

ዘሌ. 17፡11

ዮሐ. 1፡29

ገላ. 2፡16

ፊል. 1፡6

1ቆሮ. 10፡13

ዳን. 7፡22

ዳን. 12፡1-2

ማቴ. 24፡27

ዳን. 2፡44

**በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የሚስተዋለውን የኃሳብ ፍሰት ይከተሉ። እንደ ክርስትያንነታችን በኢየሱስ ሊኖረን ስለሚችለው ተስፋ ጥቅሶቹ ባንድነት የሚነግሩን ምንድነው?**

*አርብ ህዳር 16* *Nov 25*

## *ተጨማሪ ሀሳብ*

መጽሐፍ ቅዱስ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ በአስደናቂ የተስፋ ቃላት የተሞላ መጽሐፍ ነው። “በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።” ዮሐንስ 16፡33 “እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።” ማቴዎስ 28፡20 “ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን” ገላትያ 3፡13 “ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።” መዝሙር 103፡12 “ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር

ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።" ሮሜ 8፡38-39 "ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች፤ በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘላለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ።" ዘፍጥረት 9፡6 "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።" 1ኛ ዮሐንስ 3፡1 " እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ፤ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም፤ እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን።" መዝሙር 100፡3 እነዚህ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ስለአምላካችን ባህሪና እርሱስለሚሰጠን ስጦታዎች ከተነገሩት ጥቂቶቹ ናቸው።

**መጽሐፍ ቅዱስ ባይገልጽልን ኖሮ ተስፋ የምናደርግበት ምን ምክንያት ይኖረን ነበር?**

## የመወያያ  ጥያቄዎች:

1. ስለ ተስፋ የሚነግሩን ሌሎች ምን አይነት ጥቅሶች አሉ? ለርስዎ የበለጠ ትርጉም የሚሰጡዎት የትኞቹ ናቸው? ለምን?
2. _ ከሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስትያን የእምነት መመሪያዎች (ዶክትሪኖች) መካከል ለርስዎ የበለጠ ተስፋ የሚሰጡዎት የትኞቹ ናቸው?
3. _ ምንም ያህል ችግሮች፣ አሳዛኝ ክስተቶችና ውጣ ውረዶች ቢኖሩም በመጽሐፍ ቅዱስ በተሰጠን ተስፋ ደስተኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ብዙ ተስፋዎች ተሰጥተውንም በተለያዩ ክስተቶች ቶሎ ተስፋ መቁረጥ የሚቀለን ለምንድነው?
4. _ "ስለ ተስፋ እምነትና እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን ይናገሩ። በክርስቶስ ተስፋ ያድርጉና ደስተኛ ይሁኑ። እርሱን ማመስገንን ይለማመዱ። ይህ ለመንፈስና ለስጋ በሽታዎቻችን ታላቅ መድሃኒት ነው።" Ellen G. White, Mind, Character and Personality, Vol.2 Pg. 492 በጌታ ተስፋችን ሙሉ ሆኖ እንዲቀጥል ምስጋና መስጠት የሚረዳንእንዴት ነው?